Amharic | አማርኛ

# የአእምሮ ጤና የኤንዲአይኤስ/ NDIS ተደራሽነት ድጋፍ (ቪክቶሪያ)

## በኤንዲአይኤስ/NDIS መተግበሪያዎች ላይ እርዳታ ለማግኘት ደጋፊ መንገድ

የብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች መድን መርሃ ግብር (NDIS) ጉልህ የሆነ የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸውን ጨምሮ አካል ጉዳተኞችን ይረዳል። ኤንዲአይኤስ/NDIS የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ እና ከማህበረሰቡ ጋር ለመገናኘት ይረዳል።

የአእምሮ ጤና የኤንዲአይኤስ/NDIS ተደራሽነት ድጋፍ የስነ-ልቦና እና ማህበራዊ እክል ያለባቸው ጎልማሶች ኤንዲአይኤስን/NDISን እንዲያስሱ ይረዳል። ሂደቱን የበለጠ ግልጽ፣ ለማሰስ ቀላል የሆነ እና የበለጠ ማስተዳደር የሚቻል እንዲሆን ከእርስዎ፣ ከቤተሰብዎ፣ ከተንከባካቢዎችዎ እና ከጤና አገልግሎቶች ጋር አብረን እንሰራለን።

### የእኛ ድጋፍ የሚከተሉትን ያካትታል

— ለኤንዲአይኤስ/NDIS መዳረሻ ጥያቄዎች ደጋፊ ማስረጃዎችን እና የመታወቂያ ሰነዶችን ማሰባሰብ

— ጠቅላላ ሓኪሞች/GPs እና የግል የአእምሮ ሐኪሞችን ጨምሮ (በፍቃድ)፣ ከጤና አገልግሎቶች ጋር ግንኙነት ማድረግ

— ከኤንዲአይኤስ/NDIS ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች የሚመለከተው ማቅረብ

— በጊዜው የውሳኔ አሰጣጥን ለመደገፍ በኤንዲአይኤስ/NDIS ከተፈለገ ተጨማሪ ማስረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት

— በሰፈሩ የአካባቢ አስተባባሪ (LAC) አገልግሎቶች (በስልክ ወይም በአካል) በማህበረሰብ ግንኙነቶች ስብሰባዎች ላይ መገኘትን መደገፍ

— የማመልከቻውን ሁኔታ በተመለከተ ከኤንዲአይኤስ/NDIS ወይም LACs ጋር መከታተል

— የኤንዲአይኤስ/NDIS ውሳኔዎችን ይግባኝ ለማለት ከልዩ ባለሙያ አገልግሎቶች ጋር እንዲገናኙ መርዳት እና ግምገማዎችን እንዲጠይቁ ምሪት መስጠት

— ለኤንዲአይኤስ/NDIS የብቁነት ድጋሚ ምዘናዎች የስነ ልቦና-ማህበራዊ እክል ላለባቸው ሰዎች መርዳት።

### የብቃት መስፈርት

— ከ65 ዓመት በታች የሆኑ ጎልማሳ ነዎት

— ጉልህ በሆነ የአእምሮ ጤና ሁኔታ ይኖራሉ

— ለ 2 ዓመት በላይ የአእምሮ ጤና እክል እንዳለብዎ በምርመራ ተረጋግጧል

— በስነልቦናዊ እና ማሕበራዊ የአካለ ጉዳት ሥር ነው እያመለከቱ ያሉት

— ማመልከቻዎን የሚደግፍ ጠቅላላ ሐኪም ወይም የሥነ አእምሮ ሐኪም አለዎት።

### እባክዎን ያስተውሉ

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢው የአእምሮ ጤና አገልግሎት የሚተዳደሩ ሰዎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከድርጅቱ ካልተለቀቁ በስተቀር ብቁ አይደሉም።

### አገልግሎቱን ማግኘት

australian community support organisation

Each

neami national Improving Mental Health and Wellbeing

**EACH**

**ስ.ቁ.** 1300 003 224
**ኢ** NDISAccess@each.com.au

**LGAs/የአካባቢ መንግሥት ስፍራዎች**
ቦሮንዳራ፣ ማንኒንግሃም፣ ሞናሽ፣ ኋይትሆርስ፣ ኖክስ፣ ማሩንዳህ፣ ሻየር ኦፍ ያራ ሬንጅስ፣ ግሬተር ዳንዲኖንግ፣ ካርዲኒያ፣ ኬሲ፣ ባንዩል፣ ዳሬቢን፣ ዊትልሲ እና ኒሉምቢክ

**ACSO**

**ስ.ቁ.** 1300 022 760
**ኢ** NDISAccess@acso.org.au

**LGAs/የአካባቢ መንግሥት ስፍራዎች**
በቪክቶሪያ ክልላዊ እና ገጠራማ አካባቢዎች ዙሪያ ያሉ ሁሉም የአካባቢ መንግስት ስፍራዎች (LGA)

**ኒአሚ ናሽናል (Neami National)**

**ስ.ቁ.** 1300 379 462
**ኢ** intake@neaminational.org.au

**LGAs/የአካባቢ መንግሥት ስፍራዎች**
ቤይሳይድ፣ ግሌን ኢራ፣ ኪንግስተን፣ ፖርት ፊሊፕ፣ ስቶኒንግተን፣ ፍራንክስተን፣ ሞርኒንግተን ፔኒንሱላ፣ ሜልበርን፣ ሙኒ ቫሊ፣ ሜሪ-ቤክ፣ ያራ፣ ብሪምባንክ፣ ህዩም፣ ማሪቢኖንግ፣ ሆብሰን ቤይ፣ ዊንደም እና ሜልተን

Interpreter **አስተርጓሚ ያለ ክፍያ በነፃ**



## ቁልፍ መልዕክቶች

| | |
|---|---|
| **ለተጠቃሚዎች ነፃ፣ ተግባራዊ እና አክብሮት የተሞላ ድጋፍ** | — በዕለት ተዕለት ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ የአእምሮ ጤና ችግሮች ካሉዋቸው ሰዎች ጋር አብሮ መራመድ።<br>— ደጋፊ ማስረጃዎችን፣ የመታወቂያ ሰነዶችን በመሰብሰብ እና ከጤና ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር በኤንዲአይኤስ/NDIS ማመልከቻዎች ማገዝ።<br>— በመዳረሻ ጥያቄዎች፣ ግምገማዎች እና የብቃት ድጋሚ ግምገማዎች ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማቅረብ። |
| **ለብቁነት እና ለግምገማዎች ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት** | — ተሳታፊዎች የኤንዲአይኤስ/NDIS መዳረሻ ጥያቄዎችን እንዲረዱ እና እንዲያጠናቅቁ ማገዝ።<br>— ተሳታፊዎችን በዳግመ ግምገማዎች፣ ግምገማዎች እና ይግባኞች ምሪት መስጠት።<br>— ቤተሰቦችን እና ተንከባካቢዎችን አስተማማኝ በሆነ፣ አክብሮት በተሞላበት እና ደጋፊ በሆነ መልኩ ማካተት። |
| **ሪፈር ለሚያደርጉ እና ለአጋሮች በስቴት/ግዛት አቀፍ የትብብር አገልግሎቶች** | — Neami፣ EACH እና ACSO በአጋርነት የቀረበ፣ በቪክቶሪያ መንግስት የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ።<br>— ለጠቅላላ ሐኪሞች፣ ለምክር ቤቶች፣ ለአካባቢው አስተባባሪዎች እና ለማህበረሰብ ድርጅቶች ግልጽ የሪፈራል መንገዶች።<br>— የኤንዲአይኤስ/NDIS ሂደትን በቀላሉ ለመረዳት እና ለማሰስ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር መስራት። |
| **አካታች እና ተደራሽ** | — በባህል እና በቋንቋ ከተለያየ ዳራ ለመጡ ሰዎች ነፃ አስተርጓሚዎች አሉ።<br>— አገልግሎቶቹ በባህል ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ለአቦርጂናል እና ቶረስ ስትሬት ደሴት ህዝቦች አክብሮት አላቸው። |
| **በጣም ለተቸገሩ ሰዎች ቅድሚያ ይሰጣል** | — ከክሊኒካዊ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ጋር ያልተገናኙ የአእምሮ ጤና ችግር ላለባቸው ሰዎች የተነደፈ።<br>— ድጋፉ የሚያተኩረው በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው እንቅፋት በሚገጥማቸው ሰዎች ላይ ነው።<br>— አገልግሎቶቹ በመረዳት እና በእንክብካቤ መንፈስ ተሳታፊዎች ባሉበት ሁኔታ ያገኟቸዋል። |
| **ለቀጣይ የገንዘብ ድጋፍ በማህበረሰብ ድምጽ በኩል መሟገት** | — የማህበረሰብ ታሪኮች እና ሪፈራሎች ፍላጎት እና ተፅእኖ ያሳያሉ።<br>— ተደራሽ፣ ሰውን ያማከለ የNDIS ድጋፍ አስፈላጊነት የሚያጎላ ለአገልግሎቱ ቀጣይነት ያለው ጠንካራ ድጋፍ። |

Each

australian community support organisation

neami national Improving Mental Health and Wellbeing